ETHIOPIAN
ENTERPRISE DEVELOPMENT

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ
ልማት

# የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ምንነት፣ ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮና በአገራችን ያለው የትግበራ ሁኔታ

## አጭር ማስተዋወቂያ

© የኮሙኒኬሽን እና ህዝብ ግኑኝነት ስራ አስፈፃሚ

2016 ዓ.ም



## የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ

## ምንነት፣ ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮና በአገራችን ያለው የትግበራ ሁኔታ፤

### የሊዝ ፋይናንስ ታሪካዊ ዳራ

ሊዝ ወይም ማከራየት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ2000 ዓመተ-ዓለም አስቀድሞ እንደተጀመረ የተለያዩ ጽሁፎች ያስቀምጣሉ፡፡ ለዚህም የሳምራዊያን ከተማ በሆነችው ጥንታዊቷ ዑር (Ur) - ደቡባዊ ሜሶፖታሚያ (የአሁኗ ኢራቅ) እ.ኤ.አ. በ1984 በሸክላ ላይ ተጽፎ (Clay Tablets) የተገኘው የመጀመሪያው የኪራይ ስምምነት / Farm Equipment Lease/ ማሳያ ተደርጎ ይጠቀሳል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ንጉስ ሀሙራቢ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1700 ዓ/ዓለም ያወጣው የባቢሎንያ የሊዝ ህግ (Code of Hammurabi) እና በፐርሺያ ግዛት (የአሁኗ ኢራን) የተገኘው የሙራሹ ቤተሰብ ሰነድ (ከ400-450 ዓ/ዓ) የሊዝን ቀደምትነት የሚያመላክቱ ሌሎች ሰነዶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

ጥንታዊያን የግሪክ፣ የሮም፣ የግብጽ፣ የፊኒሺያንስ ስልጣኔዎች መገልገያዎችን፣ መሬት እና የቁም እንስሳትን በሊዝ ይገበያዩ የነበረ ሲሆን በተለይ ደግሞ ፊኒሺያንስ (Phoenicians) በወቅቱ “Ship Charter” ብለው በሚጠሩት የረዥም ጊዜ ስምምነት ሙሉ ዋጋቸውን በሂደት የሚከፍሉበትን ግዴታ በመግባት መርከቦችን

ይጠቀሙ የነበረ መሆኑ ከአሁኑ የ"ኢኪዩፕመንት ሊዝ" አሰራር ጋር ያመሳስለዋል፡፡

ለሀብቶች ባቡር እና ሃዲዱን ከአምራች ኩባንያዎች ገዝተው ለደንበኛው (Railroad administrator) በረዥም ጊዜ የሊዝ ስምምነት ዋናውን እና ወለዱን በኪራይ መልክ እንዲከፍልና ባለቤት እንዲሆን በማድረግ በአውሮፓ፣ በካናዳ እና በአሜሪካ ለባቡር ትራንስፖርት መስፋፋት ሊዝ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ በ19ኛው ክ/ዘመን በግብርና፣ በማምረቻ እና በትራንስፖርት ኢንዱስትሪው ውስጥ የተፈጠሩ ቴክኖሎጂዎች መብዛት እና በ20ኛው ክ/ዘመን የመጀመሪያ አስርት ዓመታት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመግዛት የነበረውን የፋይናንስ ችግር ተከትሎ ሊዚንግ የንብረት/ቴክኖሎጂ ማፍሪያ መንገድ ተደርጎ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የቤል ቴሌፎን ካምፓኒ የሚያመርታቸውን መገልገያዎች (Appliances) የሚሠጠው በሊዝ ብቻ ነበር፡፡

ሊዝ ወይም ማከራየት በአጀማመሩ ቀደምት ይሁን እንጂ ዘመናዊ መልክ በመያዝ ከአምራቾች የሽያጭ ቴክኒክነት ራሱን ወደ ቻለ የፋይናንስ አገልግሎትነት የተሸጋገረው እ.ኤ.አ. በ1952 በአሜሪካ የተቋቋመውን የመጀመሪያውን የሊዝ ኩባንያ ተከትሎ እንደሆነ ይነገራል፡፡ የሊዝ ኢንዱስትሪው በ1960ዎቹ ወደ አውሮፓና ጃፓን ከዛም ወደ ካናዳ ከ1970ዎቹ አጋማሽ ጀምሮም በማደግ ላይ ወደሚገኙ ሌሎች ሃገሮች በመስፋፋት በ1994 ሊዚንግ ከ80 በላይ በሆኑ አገሮች መስፋፋት ችሏል፡፡ ሊዝ በ21ኛው ክ/ዘመን በአደጉት አገራት ኢኮኖሚ ውስጥ ከሚደረገው ኢንቨስትመንት ከ30-40% ድርሻ አለው፡፡

የዓለም ባንክ እ.ኤ.አ. በ2018 የዓለም አገራት የነበራቸውን ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት(GDP) መሰረት አድርጎ ባወጣው መረጃ ጃፓንና ዩናይትድ ኪንግደም ቦታ ከመቀያየራቸው ውጭ በሊዝ ቀዳሚ የሆኑት አገራት በጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርትም ከአንድ እስከ አምስት ያለውን ደረጃ ያስከልካይ መያዛቸውን እንዲሁም በዚሁ ሪፖርት መሰረት በሊዝ የተሻለ እንቅስቃሴ ያላቸው አፍሪካ አገራት በጠቅላላ አገር ውስጥ ምርት ደረጃ ቀዳሚ ከሆኑ አምስት የአፍሪካ አገራት አራቱን ቦታ ይዘው ስናይ ውጤቱ ለሊዝ ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣታቸው የመጣ ነው ለማለት ባይዳዳንም በሊዝ የቴክኖሎጂ አቅማቸውን ማሳደጋቸው ለጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገቱ የማይናቅ ሚና ሳይኖረው እንደማይቀር ግምት መውሰድ እንችላለን፡፡

በአሁኑ ሠዓት የመሳሪያ ኪራይ (ሊዚንግ) በካፒታል ዕቃ ኪራይ ሂደቱ ድርሻ ያላቸው አምራቾች፣ አከራዮች፣ ባንኮች፣ ብሮከሮች፣ ትራንስፖርተሮች፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎችና

አቅራቢዎች ግንባር ፈጥረውና ማህበር (Association) ጭምር አቋቁመው በጋራ የሚመሩት የትሪሊዮን ዶላር ቢዝነስ መሆን ችሏል፡፡ የተለያዩ ያደጉና በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ሊዝን እንደየአገራቸው ነባራዊ ሁኔታ በመቃኘት እየተጠቀሙበት ሲሆን አሜሪካን ለአብነት ወስደን ብንመለከት ካምፓኒዎች ከሚጠቀሙባቸው ኢኪዩፕመንቶች ውስጥ 1/3ኛ የሚሆኑት በሊዝ ፋይናንስ የተደረጉ ናቸው፤ ከ10 ካምፓኒዎች 8 የሚሆኑት በስራቸው ቀዳሚ ሆኖ ለመገኘት ፊታቸውን ወደ ሊዝ ተጠቃሚነት ያዞራሉ፤ በቀን እስከ 20,000 የሚደርሱ የሊዝ ስምምነቶች ይፈረማሉ፡፡ ከዚህም ሊዝ በአደጉት አገራት ጭምር ከፍተኛ ቦታ እንዳለውና ለዕድገታቸውም መሰረት እንደሆነ መውሰድ ይቻላል፡፡ እንደ አጠቃላይ ሊዝ በኢኮኖሚያቸው ውስጥ ይህን ያህል ከፍተኛ ቦታን መያዝ የቻለው ምን ጠቀሜታ ስላለው ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል፡፡ ለመነሻ ይሆናችሁ ዘንድ ካነበብነው ጥቂት ለማካፈል ወደድን፡፡

## የሊዝ ፋይናንስ ጠቀሜታ

ይህ አሰራር ለተጠቃሚዎች የጎላ ፋይዳ እንዳለው የየሀገራቱ ልምድ ያሳያል፡፡ ለተከራይ ከሚሠጣቸው ጠቀሜታዎች መካከል:-

- ለማምረቻ መሳሪያ ግዢ ከፍተኛ ገንዘብ ሳያወጣ መሳሪያውን የሚያገኝበት ሁኔታ መኖሩ (100% Finance)፤
- ያለውን ውስን ገንዘብ ለሌሎች ወጪዎች መሸፈኛ ለመጠቀም ዕድል መፍጠሩ /Saves Cash/፤
- ድርጅትን በወቅቱ ቴክኖሎጂ ለማደራጀት ማስቻሉ / Keep Up-to-date/፤
- በመሳሪያው በማምረት ከሚገኘው ገቢ በየጊዜው በተከፋፈለ መጠን ለመክፈል የሚያስችል መሆኑ (Accelerates ROI)፤
- የድርጅቱን የገንዘብ ፍሰት መሰረት በማድረግ ክፍያን ለማስተካከል ዕድል የሚሠጥ መሆኑ (Customizes your terms based on cash flow)
- ከማምረቻ መሳሪያ ግዥ ጋር የተያያዙ የአስተዳደር ውጣ ውረዶች በአከራዩ በኩል ስለሚያልቁ ለተከራዩ ጫና መቀነሱ (Outsources Asset Management)፤
- በራስ አቅም ቆጥቦና አቅም ፈጥሮ ለመግዛት በሚጠይቀው ጊዜ ውስጥ ከሚፈጠር የዋጋ ግሽበት መጠበቁ (Hedges Against Inflation) የሚሉትን መውሰድ ይቻላል፡፡

## የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ በአገራችን

የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣትና ሀገራችንን በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ለኢንዱስትሪ ልማቱ ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ መፍታት የግድ ይላል፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ በተለይም የአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዝ ዘርፉ ካሉበት ማነቆዎች መካከል አንዱ የሆነውን የማምረቻ ቴክኖሎጂ ችግር ለመፍታት የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በመውሰድ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አሰራር በአገራችን ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ይሁን እንጂ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ድጋፉ በምን ያህል መጠን በአምራች ኢንተርፕራይዞችና አዲስ ወደ ዘርፉ መግባት በሚፈልጉ አካላት ይታወቃል? አከራይ ተቋማቱስ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ያለባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች አስቀድሞ በማዘጋጀትና ተጠቃሚ ሊሆኑ ለሚችሉ አካላት ተደራሽ በማድረግ ረገድ ምን ያህል ገፍተው ሄደዋል? በሂደቱ ሚና ያላቸው ሌሎች ፈጻሚና ባለድርሻ አካላትስ ምን ያህል በቂ ግንዛቤ ይዘው ተቀናጅተውና ተደጋግፈው ይሠራሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ ለአንባቢያንና ለዘርፉ ተዋንያን ትተን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ድጋፉ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ዕድገትና ተወዳዳሪነት ላይ ሊኖረው የሚችለውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተግባራዊነቱ ርብርብ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን ከአገራችን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ድጋፍ አኳያ መሰረታዊ በሆኑና ለተጠቃሚዎችና ለድጋፍ ሠጪ አካላት ቢደርሱ ብለን ባሰብናቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ በማትኮር መረጃዎችን እንደሚከተለው ለማቅረብ ሞክረናል፡፡

በአገራችን የካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ስራ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 103/1990) የወጣው በ1990 ዓ/ም ቢሆንም ከአጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ (Operating lease) ባለፈ በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ላይ ትኩረት አድርጎና ፈቃድ አውጥቶ ወደ ስራ የገባ ተቋም ባለመኖሩ ቀድሞ የወጣው አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 807/2005 ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ በማሻሻያው መሰረት፡-

በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ/ኪራይ አሰራሩ የሚቀርብ የካፒታል ዕቃ (አክሰሰሪዎችን ጨምሮ ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ማንኛውም መሳሪያ ወይም ማሽን) ፡-

- ☞ ከውጭ ሲገባ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ መሆኑ፤
- ☞ ተከራዩ ለአከራይ ክፍያ በሚፈጽምበት ጊዜ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ (VAT) የማይከፍል መሆኑ፤

☞ የካፒታል ዕቃውን ያለ ተጨማሪ ዋስትና(ራሱ ማምረቻ መሳሪያው ዋስትና ሆኖ) በኪራይ መጠቀም መቻሉ ዘርፉን ለማበረታታት በመንግስት ከሚሰጡ የማበረታቻ ድጋፎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ማሻሻያውን ተከትሎ በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አሰራሩ የካፒታል ዕቃዎችን በኪራይ ለማቅረብ በአራት ክልሎችና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቋቋሙ 5 የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበራት ከ2008 ዓ/ም ጀምሮ በስራ ላይ የሚገኙ ከመሆኑም ባሻገር የኢትዮጵያ ልማት ባንክም ተመሳሳይ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን ዘግየት ብሎም ድሬ ማይክሮፋይናንስ የሊዝ አገለግሎቱን ተቀላቅሏል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ከላይ የጠቀስናቸው ተቋማት የካፒታል ዕቃ እያቀረቡ ያሉት በዱቤ ግዥ (Hire purchase) ሞዳሊቲ ሆኖ ይህም አከራይና ተከራይ ባደረጉት ስምምነት መሰረት አከራይ በተወሰነ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ እየተከፈለው አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃ ተከራዩ እንዲጠቀምበት የሚፈቅድበት አሰራር ሲሆን እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተደረገ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ ለተከራዩ የባለቤትነት መብት የሚተላለፍበት ተከራዩ የመጨረሻውን ክፍያ እንደፈጸመ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ወዲያውኑ የሚያገኝበት የኪራይ ዓይነት ነው፡፡



## የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

በቀጣይ በአከራይ ተቋማቱ ሲደረጉ የሚችሉ ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆኖ አምራች ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን የሚከተሉትን ዋና ዋና መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል:-

- የንግድ ስራ ፈቃድ
- የንግድ ዕቅድ ወይም የአዋጭነት ጥናት
- የመሳሪያው ዝርዝር መግለጫ (Specification)
- ከ15-20 በመቶ ቅድመ-ክፍያ
- መሰረተ-ልማት የተሟላለት የማምረቻ ቦታ (በመንግስት በተመቻቸ ቦታ፣ በግል ይዞታ ወይም በኪራይ) ያላቸውና ቦታው በኪራይ የተገኘ ከሆነ የኪራይ ውል ማቅረብ
- የዋጋ ማቅረቢያ ደረሰኝ (Pro-forma invoice)
- ለካፒታል ዕቃው የመድህን ሽፋንና ዕድሳት ወጪን ለመክፈል ፈቃደኝነት
- ካፒታላቸው ከ500 ሺህ እስከ 15 ሚሊዮን የሆኑ (በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለሚሰጥ አገልግሎት ብቻ)
- ነባር ከሆኑ ሂሳባቸውን በማስመርመር የኦዲት ሪፖርትና የግብር ግዴታቸውን መወጣታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ
- መልካም የተበዳሪነት ታሪክ ያላቸው

## የካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት ዓይነቶች

በአገራችን የካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስን ሥርዓትን እንዲተገብሩ በብሔራዊ ባንክ ፍቃድ የተሰጣቸው ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ለካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ አክስዮን ማሕበራት ሲሆን በቀጣይ ለተለያዩ ባንኮች እና ተቋማት የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ የተፈቀዱ የኪራይ ዓይነቶችም የዱቤ ግዢ / Hire Purchase/ እና የፋይናንስ ኪራይ ናቸው፡፡ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የካፒታል ዕቃ ባለቤት ለማድረግ በዋነኝነት በዱቤ ግዢ ሥርዓት የሚተገበር ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ የፋይናንሺያል (Financial) ኪራይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡

## የዱቤ ግዢ / Hire Purchase/

ይህ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ዓይነት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ስራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 በተፈቀደውና በአዋጅ ቁጥር 807/2005 በተደረገው ማሻሻያ መሰረት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ አይነት ሆኖ አከራይና ተከራይ ባደረጉት ስምምነት መሰረት አከራይ በተወሰነ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ እየተከፈለው አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃ ተከራዩ እንዲጠቀምበት የሚፈቅድበት አግባብ ይኖረዋል፤ እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተፈጸመ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ የባለቤትነት መብት እንዲሁም የመጨረሻ የኪራይ ክፍያ እንደተፈጸመ ወዲያውኑ የካፒታል ዕቃው ሙሉ በሙሉ የባለቤትነት መብት ለተከራዩ የሚተላለፍለት ይሆናል፡፡

## የፋይናንሺያል ኪራይ /Financial Lease/

የፋይናንሻል የኪራይ ስምምነት ተከራዩ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ የካፒታል ዕቃውን በአግባቡ እንዲጠቀምበት የውል ስምምነት ይገባል፤ ተከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ምንም አይነት የባለቤትነት መብት የለውም፤ ስምምነቱ ውል የተገባለትን ሙሉ ዋጋ በኪራይ ተከፍሎ የሚሸፈንበትና ሊሰረዝ የማይችል ስምምነት ነው፤ የስምምነቱ ጊዜ ሲያበቃ ሁለቱ ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ በስምምነቱ መሠረት የካፒታል ዕቃውን ይረከባል፤ ካልተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ለአከራዩ ይመልሳል፡፡

የካፒታል ዕቃው በተገቢው መንግስታዊ ኣካል ይመዘገባል፤ አቅራቢው ከሰጠው የጥገና ዋስትና/ warranty/ Guaranty/ ጊዜ በኋላ የጥገና ተግባራት የማከናወን ሃላፊነት የተከራይ ነው፡፡

## የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የሚተገበርባቸው የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች

- ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ ሽመናና ስጋጃ ሥራ
- የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ሥራ
- የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ሥራ
- አግሮ ፕሮሰሲንግ
- የኬሚካል ውጤቶች
- የኮንስትራክሽን ግብዓት

## የካፒታል ዕቃ ዓይነትና አቅራቢ ድርጅት መለየት

የካፒታል ዕቃ አቅራቢዎች ሦስት ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በሀገር ውስጥ ዕቃዎችን የሚያመርቱ አቅራቢዎች፡- በቅድሚያ ሀገር ውስጥ አምራችና አቅራቢዎች የሚመረቱና የሚቀርቡ የካፒታል ዕቃዎችን በመለየት እንዲመረት/ እንዲቀርብ ይደረጋል፤

አስመጪ አቅራቢዎች፡- በሀገር ውስጥ የማይመረቱ ሆነው የአምራች ኢንዱስትሪዎቹ ፍላጎት መሠረት በማድረግ በአስመጪ አቅራቢዎች የሚቀርቡ የካፒታል ዕቃዎችን በግዢ መመሪያ መሠረት በመጋበዝ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

የውጭ አገር አቅራቢ/አምራች፡- በሀገር ውስጥ የማይመረቱና መገኘት የማይችሉ መሆኑ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ ህጋዊ ፍቃድ ያላቸውንና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸውን ተቋማት በግዥ መመሪያው መሠረት በመጋበዝ የካፒታል ዕቃን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

በዚህ ደረጃ አከራዩ ተከራይ የሚፈልገውን የማምረቻ መሳሪያ ዓይነት በመምረጥና አቅራቢዎችን በመለየት ሂደት እንዲሳተፍ ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡ ይሁንና የካፒታል ዕቃ ጥራትና ብቃት ለቢዝነሱ ቀጣይነት መረጋገጥ እንደ ዋስትናም ጭምር የሚያገለግል በመሆኑ፣ በተለይ የመሳሪያ ዓይነቱን የመለየትና ደረጃውን የመምረጥ ለተከራይ የመወሰን መብት የሚሰጠው ሲሆን የአቅራቢን የመለየት ተግባር ግን በካፒታል እቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አማካኝነት የግዢ ስርዓቱን መሰረት በማድረግ በጋራ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## የመሳሪያ ኪራይ ውል ስምምነት

በቢዝነስ ፕላን ወይም በአዋጭነት ጥናት መሰረት የመሳሪያው ዓይነት ተገምግሞ ከጸደቀ በኋላ ተከራይና አከራይ የመሳሪያ ኪራይ ውል ስምምነት ያደርጋሉ፡፡ የውል ስምምነቱ ሰነድ በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ የሚዘጋጅ ሲሆን በዋናነት በመሳሪያ ግዢ መወዳደሪያ ላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር ሁኔታዎች ያካተተ መሆን ይገባዋል፡፡

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ኪራይ የማሰባሰብ ተግባር በወቅቱና በውሉ መሰረት ይከናወናል የአከፋፈል ስርአቱ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

የኪራይ ክፍያ ጊዜ፡- እንደ ፕሮጀክቱ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት እና የካፒታል ዕቃው የአገልግሎት ጊዜ (economic life of the capital goods) የሚወሰን ሆኖ ከፍተኛው የመክፈያ ጊዜ ከ5-7 ዓመት ይሆናል፡፡

የኪራይ ክፍያ ሥርዓቱ በተወሰነ ጊዜያት ወይም በየወሩ ወይም በየሦስት ወሩ የሚፈጸም ሆኖ እንደሥራው ባህሪ በየስድስት ወሩ የአከፋፈል ሥርዓት አለው ፡፡

ወለድ፡- የወለድ መጠን እንደ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ዕቃ አቅራቢ አከራዩ የሚወሰን ይሆናል፡፡ በተከራዩ ላይ ወለድ /ኪራይ መሰላት የሚጀምረው መሳሪያው ተተክሎ ስራ ከጀመረበት ግዜና ውል ከተያዘ ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፤ ይህ ወለድ በቀሪ ሚዛን ላይ የሚሰላ /Declining Balance/ ይሆናል፡፡ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚዎች ለሚሰጣቸው አገልግሎት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አይጠበቅባቸውም፡፡

የእፎይታ ጊዜ፡- የእፎይታ ጊዜ እንደየስራ መስኩ (ምርት አምርቶ ለገበያ ለማድረስ ከሚጠይቀው ጊዜ አኳያ) የሚለያይ ሆኖ ይህም ማሽኑ ተተክሎ ማምረት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከፍተኛው ጊዜ 6 ወር ይሆናል፡፡



## የካፒታል ዕቃ ግዢ ስለማከናወን

- ተከራይ ቅድመ-ክፍያ ማስቀመጡ ከተረጋገጠ በኋላ በተዘጋጀውና ተከራይና አከራይ በተስማሙበት ስፔስፊኬሽን መሰረት ለአቅራቢው የግዢ ወይም የስራ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
- በዚህ ወቅት የካፒታል ዕቃውን የሚያስረክብበት ቦታ በግልጽ መገለጽ ይኖርበታል፡፡
- ስለ ካፒታል ዕቃው ደህንነት ዋስትና ጉዳይና ከግዢ በኋላ ያሉ አገልግሎቶችና ጥገና ስራዎች አቅራቢውና አከራይ በጋራ በሚገቡት ውል መሠረት ይተገበራል፡፡

## በግዢ የሥራ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት፡-

- ለሥራው አስፈላጊ የሆነውን የካፒታል ዕቃ የመምረጥ በዋነኛነት በተከራይ ሆኖ በጋራ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ ጋር የሚከናወን ሲሆን አቅራቢውን የመለየት ተግባር የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ ይሆናል፡፡
- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተከራይ የራሱን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የካፒታል ዕቃውንና የካፒታል ዕቃ አቅራቢ በነፃነት የመምረጥ መብት ቢሰጠውም የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ ለኪራይ የሚውለው የካፒታል ዕቃ ለቢዝነሱ ጥራትና ቀጣይነት እንደ ዋስትና ስለሚያገለግል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስፔሲፊኬሽን ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
- አቅራቢዎችና አምራች ድርጅቶች በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም በኩል በቀረበላቸው ስፔስፊኬሽን መሰረት የካፒታል ዕቃውን እስከነመለዋወጫ ዕቃዎቹ መዘጋጀቱን እንዲሁም የተከላና የሙከራ ጊዜ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ ጋር በተደረገው ስምምነት መሰረት የሚያከናውኑ መሆን አለባቸው፡፡
- አቅራቢዎች መልካም ስም ያላቸው፣ በቂ የዋስትና ጊዜ የሚሰጡና ቀና ትብብር ለማድረግ ዝግጁ የሆኑ እንዲሁም በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡
- ተከራዩ ቅድመ ክፊያ ከከፈለ በኋላ የካፒታል ዕቃውን ለመረከብ የሚወስደው ጊዜ ከ6 ወራት መብለጥ የለበትም፡፡

የካፒታል ዕቃ መግዣ መጠን:- ለአንድ ተጠቃሚ የሚገዛው የካፒታል ዕቃዎች አጠቃላይ መግዣ ዋጋ ዝቅተኛው መጠን ከብር 50,000 (አምሳ ሺህ) ማነስ የለበትም:: ከፍተኛውን ጣሪያ በተመለከተ ለካፒታል እቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበራት የካፒታላቸውን እስከ 2.5 በመቶ ድረስ (በአሁኑ ሰዓት እስከ 10 ሚሊዮን ይደርሳል)ሲሆን ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ ደግሞ ከሁለት ሚሊዮን (2,000,000) እስከ ስልሳ ሚሊዮን (60,000,000) ሆናል:: በቀጣይ አገልግሎቱን ለሚሰጡ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በብሄራዊ ባንክ የሚወሰን ይሆናል::

## መሳሪያ ማጓጓዝና ምዝገባ ስለ ማከናወን

መሳሪያ ማጓጓዝ:-የመሳሪያ ርክክብ ስርአቱ የተከራይ የስራ ቦታ ድረስ እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን አቅራቢ በራሱ ማጓጓዣ ማቅረብ ይኖርበታል:: ሆኖም ግን የተከራይ የስራ ቦታ ዝግጅት ያልተጠናቀቀ ከሆነና በተከራይና አከራይ ስምምነት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ በሚያዘጋጁት መጋዘን እንዲቀመጥና ርክክብ እንዲፈጸም ይደረጋል::

## በርክክብ ወቅት

- የካፒታል ዕቃው በስፔስፊኬሽን መሰረት የቀረበ መሆኑን፣
- መለያ ቁጥሩ ትክክል መሆኑን፣
- በውሉና በስምምነቱ መሰረት አክሰሰሪና መለዋወጫ መኖራቸውን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ በማረጋገጥ ርክክብ ይካሄዳል::

## የካፒታል ዕቃ ምዝገባ

- በኪራይ የሚሰጡት የካፒታል ዕቃዎች በአገልግሎት ሰጪው ስም የሚገዙ ሆኖ ሕጋዊ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ እና በምዝገባ ወቅት የተሰጠው መለያ ቁጥር እንዲኖረው ተደርጎና ስልጣን በተሰጠው አካል መመዝገቡን በማረጋገጥ ርክክብ እንዲፈፀም ይደረጋል::

- የካፒታል ዕቃ ምዝገባ የሚከናወነው ያለበትን እዳ ከፍሎ ሳይጨርስ መሳሪያው እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ እንዲሁም ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ለማድረግ ነው:: ምዝገባውም በየደረጃው ስልጣን በተሰጠው አካል የሚከናወን ይሆናል::
- የካፒታል ዕቃውን ያስመዘጋቢው አካልና ያለ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ ዕውቅና ከቦታ ወደ ቦታ ማዘዋወር አይቻልም::

## ኢንሹራንስ መግባት፣ የውል ምዝገባ ስለማከናወንና ስለማስተላለፍ

የካፒታል ዕቃው በአዋጅ ቁጥር 103/1990 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1(መ) እና 3(ሐ) መሰረት ኢንሹራንስ እንዲገባለት ይደረጋል:: በዚሁ መሰረት የኢንሹራንስ ወጪው በተከራይ የሚሸፈን ይሆናል::

- ይህ ተግባር የሚከናወነው በርክክብ ወቅት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በጋራ ከሚሰራው የኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ይሆናል::
- ለማምረቻ መሳሪያዎች የሚገባው ኢንሹራንስ አይነት የእሳት አደጋ ሽፋን እንዲኖረው ይደረጋል::

ተጠቃሚኢንተርፕራይዙ የኢንሹራንስ ክፍያውን መክፈል ካልቻለ ከራዩ ክፍያውን በመክፈል የኪራይ ዋጋው ላይ በማሰብ የሚያስከፍል ይሆናል:: የካፒታል ዕቃ ለተጠቃሚዎች ከመተላለፉ በፊት ተከላና የሙከራ ምርት በአቅራቢው ድርጅት በኩል መከናወኑን በአከራዩና በአማካሪ ድርጅት የሚረጋገጥ ይሆናል::

## የካፒታል ዕቃ አጠቃቀም ሥልጠና መስጠት፣ ጥገናና ዕድሳት

ሀ/ የካፒታል ዕቃ አጠቃቀም ስልጠና

- በፒታል ዕቃ ኪራይ ውል መሰረት ንብረቱን የሚጠቀምበት ተከራዩ በመሆኑ የካፒታል ዕቃውን በጥንቃቄ ይዞ መጠቀም፣ ተከታታይ ጥገናና እድሳት ማድረግ አለበት:: ይህንን ደንበኛው (ተካራዩ) አውቆትና ተረድቶት በኪራዩ ውል ውስጥ ተካቶ ደንበኛው እንዲፈርም ይደረጋል::
- የካፒታል ዕቃ አቅራቢው በውሉ መሰረት ስለካፒታል ዕቃ አጠቃቀምና ጥገና ስልጠና እንዲሰጥ ይጠበቅበታል::

## ለ/ የካፒታል ዕቃ ጥገናና እድሳት

- ተከራዩ በተሰጠዉ የካፒታል እቃዉ አጠቃቀም ማኑዋል መሠረት እቃዉን መጠቀም አለበት፡፡ ለዚሁም ተገቢዉን ስልጠና እንዲሰጠዉ ይደረጋል፡፡
- ጥገናና እድሳት በሚደረግበት ወቅት ከካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ እውቅና ውጪ ከቦታ ወደ ቦታ ማንቀሳቀስ  አይፈቀድም፡፡
- የዋስትና ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ያለዉን ጥገና አቅራቢ ተቋሙ በራሱ የሚያከናዉን ሲሆን የዋስትና ጊዜ ካበቃ በኋላ ለሚደርሱ ብልሽቶች ለጥገናና ዕድሳት የሚወጣው ወጪ በተከራዩ የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ይህም በውሉ ሳይ በግልጽ ተካትቶ ደንበኛው እንዲፈርም ይደረጋል፡፡
- የጥገናና እድሳት ደረጃው ቀላል ከሆነ ተከራዩ ጥገናና እድሳት የሚደረግበትን ቦታ፣ ለጥገናና እድሳቱ የጠየቀው ወጪና በየትኛው ቦታ ጥገናና እድሳት እንደሚደረግለት ለፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በወቅቱ ማሳወቅ አለበት፡፡
- ከባድ የሆነ ጥገናና ዕድሳትን በተመለከተ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙና ኢንተርፕራይዙ በጋራ በሚመርጡት ቦታ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡



## የቃላት መፍቻ

"ማከራየት" ማለት አከራይ አንድን የካፒታል ዕቃ በፋይናንስ ኪራይ ወይም በዱቤ ግዥ ስምምነት መሰረት ያለምንም መያዣ በተወሰነ ክፍለ-ጊዜ የሚፈጸም ክፍያ እየተቀበለ ተከራዩ ለተወሰነ ጊዜ ለምርትና አገልግሎት መስጠት ዓላማ እንዲጠቀምበት የሚፈቀድበት በዓይነት የሚደረግ የፋይናንስ አቅርቦት ነው፡፡

"አከራይ" ማለት በውል ስምምነቱ መሰረት አንድን የካፒታል ዕቃ በፋይናንስ ኪራይ ወይም በዱቤ ግዥ ለተወሰነ ጊዜ በኪራይ የመጠቀም መብት የሚሰጥ አካል ነው፡፡

"ተከራይ" ማለት በውል ስምምነት መሰረት የካፒታል ዕቃን በፋይናንስ ኪራይ ወይም በዱቤ ግዥ ለተወሰነ ጊዜ ከአከራዩ በኪራይ ክፍያ የመጠቀም መብት ያገኘ አካል ነው፡፡

"የኪራይ ክፍያ" ማለት ተከራዩ ከአከራዩ ለተከራየው ዕቃ በተስማሙበት የኪራይ ዋጋና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚከፈል የገንዘብ መጠን ነው፡፡

"የፋይናንስ ኪራይ" /financial lease/ ማለት አከራዩ ቀደም ሲል ይዞት የሚገኘውን የካፒታል ዕቃ፤ ወይም በተከራዩ መራጭነት አቅራቢ ተብሎ ከሚጠራው ሦስተኛ ወገን የሚገዛውን የካፒታል ዕቃ ተከራዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ በሁለት ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ክፍያ በተወሰነ ጊዜ በመፈጸም እንዲጠቀምበት የሚያከራይበት፣ የኪራይ ስምምነት ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ይዞ የሚቆይበትና የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ሊገዛ የሚችልበት የኪራይ ዓይነት ነው፡፡

የዱቤ ግዥ (Hire purchase) አከራይና ተከራይ ባደረጉት ስምምነት መሰረት አከራይ በተወሰነ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ እየተከፈለው አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃ ተከራዩ እንዲጠቀምበት የሚፈቅድበት፣ እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተደረገ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ ለተከራዩ የባለቤትነት መብት የሚተላለፍበትና ተከራዩ የመጨረሻውን

ክፍያ እንደፈጸመ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ወዲያዉኑ የሚያገኝበት የኪራይ ዓይነት ነው፡፡

“የካፒታል ዕቃ” ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ማንኛውም መሳሪያ ወይም ማሽን ሲሆን አክሰሰሪዎችንም ይጨምራል፤

“የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ” ማለት የፋይናንስ ኪራይና የዱቤ ግዥን ያጠቃልላል፡፡

አቅራቢ፡- ማለት ከአከራይ ወይም ተከራይ ሌላ ሆኖ የካፒታል ዕቃዎችን በመሸጥ ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፡፡

መልሶ መውሰድ፡- ማለት የካፒታል ዕቃ ተከራዩ ግዴታውን በአግባቡ ሳይወጣ ሲቀር አከራዩ የካፒታል ዕቃውን መልሶ መረከብ ማለት ነው፡፡

መልሶ መረከብ፡- በፋይናንሺያል ኪራይ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን በመከራየት ክፍያውን ካጠናቀቀ በኋላ የካፒታል ዕቃውን ለመውሰድ ካልተስማማ አከራዩ ዕቃውን መልሶ መውሰድ ማለት ነው፡፡

ሊሰረዝ የማይችል ሰምምነት፡- ማለት በህግ አፈጻጸም ወይም በስምምነት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ሊሰረዝ የማይችል የኪራይ ስምምነት ማለት ነው፡፡

ኢንሹራንስ፡- ማለት አንድ የካፒታል ዕቃ አደጋ ቢደርስበት ወይም አደጋ ሲያደርስና ጉዳት ሲከሰት ለጉዳቱ ካሳ የሚከፍል የመድን ሥርዓት ነው፡፡

“መዝጋቢ አካል” ማለት እንደ አግባቡ ንግድ ሚኒስቴር ወይም የካፒታል ዕቃዎችን እና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶችን የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፡፡

“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47/1/ የተመለከቱትን ክልሎች ማለት ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ ድሬዳዋ መስተዳድርንም ይጨምራል፡፡

“ከተማ” ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም 2 ሺህ ወይም ከዚህ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡

“የከተማ አስተዳደር” ማለት ቻርተር ያላቸውን ከተሞች ሳይጨምር በሌሎች ከተሞች ውስጥ እንደ ማዘጋጃ ቤት ያለ የከተማ አስተዳደርና አገልግሎት እንዲሰጥ የተቋቋመና ራሱን የቻለ አስተዳደራዊ አካል ነው፡፡

”የክልል ኤጀንሲዎች/ ቢሮዎች” ማለት በየክልሉ የተዋቀሩ የአነስተኛ እና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዝ ልማትን የሚደግፉና የሚያስተባብሩ ኤጀንሲዎች/ ቢሮዎች ማለት ነው::

የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት ማለት በየከተማው በምርት ስራዎች ላይ ለተሰማሩና በተወሰነ አካባቢ ተሰባስበው አንድ ዓይነት ወይም ተመጋጋቢ ምርቶችን በማምረት በጋራ ተጠቃሚ ለመሆን የሚሹ ኢንዱስትሪዎችን ለማስተሳሰርና ለመደገፍ የተደራጁ ናቸው፡፡

“ክላስተር” ማለት በአንድ አካባቢ የተሰባሰቡና ቁጥራቸው ከ30 በላይ ሆኖ በ40 ኪ/ ሜትር ወይም በ1 ሰዓት የመኪና ጉዞ ርቀት ላይ የሚገኙ ኢንተርፕይዞች ሆነው ተመጋጋቢ የምርት፣ የአገልግሎትና የግብዓት አቅርቦት ትስስር ያላቸውና ተመሳሳይ ስጋትና መልካም አጋጣሚውንም የሚጋሩ ተቋማት ስብስብ ነው::

“ማኑፋክቸሪንግ“ ማለት ማሽንን፣ መሳሪያን ወይም ጉልበትን በመጠቀም በጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው ምርት ማምረት ነው፡፡

“አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ” ማለት ከ 11 (አስራ አንድ) እስከ 50 (ሃምሳ) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 600,001 (ስድስት መቶ ሺህ አንድ) እስከ ብር 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

“መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ” ማለት ከ 51 (ሃምሳ አንድ) እስከ 100 (መቶ) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 10,000,001 (አስር ሚሊዮን አንድ) እስከ 90,000,000 (ዘጠና ሚሊዮን) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

ስካን ያድርጉት

© የኮሙኒኬሽን እና ህዝብ ግኑኙነት ስራ አስፈፃሚ

አድራሻ፡ ቡልጋሪያ ማዞሪያ አካባቢ ሮማን ህንፃ

ስልክ፡ +25115521001/ +251115150333

Email: ethiopianenterprise@gmail.com

eed@eed-sme.com

Ethiopian Enterprise Development

Beminet printing press plc